# ኤፍ ኤሞቻችንን መልሱልን

ትናንትና በአንድ የኤፍ ኤም ራድዮ የሚተላለፍ ፕሮግራም ታክሲ ውስጥ ሆኜ እየሰማሁ ነበር፡፡ «ጋዜጠኛው» ቀብሩ በትናንትናው ዕለት ስለተፈጸመ አርቲስት ተናገረና «rest in peace ብለናል» አለ፡፡ የአፍ ወለምታ ወይንም ልማድ ነው ብዬ ዝም አልኩ፡፡ አሁንም ስለ ሌላ ስለ ዐረፈ ሰው ተናገረና ያንኑ ደገመው፡፡ ይኼኔ ደነገጥኩ፡፡ ይኼ የኤፍ ኤም ሬዲዮ በአማርኛ ቋንቋ ለሕዝበ ኢትዮጵያ የሚተላለፍ ፕሮግራም ነው፡፡ አሁን «ነፍስ ይማር» የሚለው የአማርኛ ቃል የሚጠፋው ጋዜጠኛ እንዴት ነው የኢትዮጵያን ሕዝብ ጉዳዮች ሊያነሣ የሚችለው? ወይስ

የኛ ሙሽራ ኩሪባቸው

በእንግሊዝ አናግሪያቸው

እንደሚለው የሠርግ ዘፈን እንግሊዝኛ ማወቅ የዕውቀት መለኪያ ነው? ለነገሩ እርሱ ምን ያድርግ «ቢሾፍቱ አውቶቡስ? ብሎ መጻፍ ሲቻል «ቢሾፍቱ ባስ» ብሎ ጽፎ በከተማዋ ውስጥ በኩራት በሚዞርባት ሀገር፣ «ልዩ ክትፎ» ማለት ሲቻል «ስፔሻል ክትፎ» «ተራ ክትፎ» ማለት ሲቻል «ኖርማል ክትፎ» ተብሎ የጉራጌ ክትፎ እንግሊዛዊ በሚሆንባት ሀገር «ነፍስ ይማር»ን አለማወቅ ነውር ላይሆን ይችላል፡፡

ይህንን እያሰላሰልኩ እነዚያኞቹ «good bye have a nice weekend» ብለው ተሰናበቱንና ሌሎች ደግሞ መጡ፡፡ ስለ ውጭ ሀገር ዘፋኞች፣ የፊልም ተዋንያን፣ ፊልሞች እና ዘፈኖች እንደሚያወሩን፣ ስለ አንዳንዶቹም ዝርዝር መረጃ እንደሚሰጡን ነገሩንና ለመሸጋገርያ ብለው የእንግሊዝኛ ዘፈን ጋበዙን፡፡

ይኼኔ ነው ኤፍ ኤም ሬዲዮኖች የማን ናቸው? እያልኩ መጠየቅ የጀመርኩት፡፡ አንድ ዓይን ያላት በዐፈር አትጫወትም ይላል የሀገሬ ሰው፡፡ ጥርስ የላት በዘነዘና ትነቀስ አማራት ብሎም ይጨምርበታል፡፡ ለራሳችን ኤፍ ኤም ሬዲዮ እና ስኳር እያጠረን ተቸግረናል፡፡ ከነዚሁም ቆርሰን ለፈረንጆቹ ከሰጠናቸው ምን ሊተርፈን ነው? ወይስ እነርሱ ለኛ ብድር እኛ ለእነርሱ ሬዲዮ ልንሰጣቸው ተስማምተናል፡፡

እስኪ በሞቴ ክፈቱ እና ስሙ፡፡ አሜሪካኖች ወይንም እንግሊዞች የሚያከብሩት በዓል ካለ ኤፍ ኤሙ በሙሉ የሚያወራው ስለ አከባበሩ ነው፡፡ የአድዋ በዓል ዕለት ብትሰሙ ግን የጣልያንኛ ዘፈን ተለቀቆ ታገኛላችሁ፡፡ ስለ ድል በዓል ምንም የማይል ሬዲዮ ስለ አሜሪካኖቹ የምስጋና ቀን እስኪበቃን ይነግረናል፡፡

እገሊት የተባለችው የአሜሪካ ዘፋኝ የምትበላው ባናና ነው፣ የምትጠጣው አፕል፣ ልብሷ ሚኒ ነው፣ ጫማዋ ቲዌንቲ ናይን ቁጥር፣ ቤቷ ማንሐተን ነው፣ አባቷ ጄምስ እናቷ አና ትባላለች፡፡ ባለፈው ሰኞ ስፒች አደረገችና ኤ ሎት ኦፍ ፒኦፕል አደነቋት፡፡

አሁን ይኼ የአማርኛ ነው ወይስ የእንግሊዝኛ ፕሮግራም? ለመሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚወራ ጠፋ? ጉዳይ ጠፋ?

ለመሆኑ ለምን ይሆን ኤፍ ኤሞቻችን ዲያስጶራ የሆኑት? ስገምተው አንድ አራት ምክንያቶች አያጣቸውም፡፡

የመጀመርያው ሀገርን የማወቅ ችግር ነው፡፡ የሀገሪቱን ባህል፣ እምነት፣ ቋንቋ እና ሃሳብ የማወቅ ችግር፡፡ እንጅ ነፍስ ይማር ጠፍቶት «ሬስት ኢን ፒስ» ማለት ከየት ይመጣል» በመገናኛ ብዙኃን የሚነገር ነገር ከልጅ እስከ ዐዋቂው የሚሰማው በመሆኑ የሀገርን ወግ፣ ባሕል እና ደረጃ መጠበቅ አለበት፡፡ አንዳንዴኮ ጠዋት የሚተላለፍ ፕሮግራም ላይ እንደ ምን ዋላችሁ» የሚል ሰላምታ ትሰማላችሁ፡፡ እንዴት ነው አንድ ሰው በእንደምን ዋላችሁ? በእንደምን አረፈዳችሁ?፣ በእንደምን አመሻችሁ? እና በእንደምን አደራችሁ መካከል ያለውን ልዩነት ሳያውቅ ጋዜጠኛ ለመሆን የቻለው? መቼም ይህቺ ሀገር መቀባት እንጂ መማር የማይጠቅምባት ሀገር እየሆነች ነው፡፡

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ያለመዘጋጀት ነው፡፡ በባህላችን እነኳንስ ሰው ፊት ለሚቀርብ ነገር ለቤተሰብ ለሚቀርብም ነገር መጨነቅ መጠበብ ልማዳችን ነበር፡፡ በሃይማኖት ትምህርታችን እንኳን አዳምን ፈጣሪ ለምን ዓርብ ቀን ፈጠረው? ሲባል ሰማይን ከነግሡ ምድርን ከነ ግሣግሡ አዘጋጅቶ አስውቦ ሊያመጣው ስለወደደ ብለው ሊቆቻችን ይነግሩናል፡፡

አንዳንድ ጋዜጠኞቻችን ግን ስለ ፕሮግራማቸው ማሰብ የሚጀምሩት ማይክራፎኑን ሲይዙ ነው መሰል፡፡ አንድ ታላቅ ሰው አንድ የኤፍ ኤም ሬዲዮ ቀርቦ የተናገረውን እዚህ ላይ ባነሣው

እንዴት ጥሩ ነው፡፡ «እኔ የሚናገረውን የሚያውቅ ወይንም የሚያውቀውን ብቻ የሚናገር ሰው እወዳለሁ» ነበር ያለው፡፡ በዚህ ዘመን ሰዎችን እያባለገ ያለ አንድ ነገር አለ፡፡ ኢንተርኔት የሚባል፡፡ ዩ ትዩብ የሚባል «መጋኛ» አለ ክበበው ገዳ፡፡ ስለ አንድ ነገር በቀላሉ ለማግኘት ካሰብክ መጽሐፍ ሳታገላብጥ፣ ሊቃውንት ሳትጠይቅ፣ መስክ ሳትወርድ፣ የዓይን ምስክር ሳትሻ፣ ማሰብ ማሰላሰል ሳያስፈልግህ ጉግልን መጎርጎር ነው፡፡

በአብዛኛው ደግሞ የሀገራችን ጉዳይ በጉግል አይጎረጎርም፡፡ መረጃዎች ሁሉ ያሉት መስኩ ላይ ነው፡፡ መውጣት መውረድ፣ መሄድ መምጣት፣ መልፋት መድከም ይጠይቃሉ፡፡ መረጃው ያለው በጥሬው ነው፡፡ አዘጋጅቶ፣ አብስሎ፣ አጣፍጦ የሚያቀርበው ጋዜጠኛ ይጠይቃል፡፡ ይህ ደግሞ የበሰለ ቀርቦለት፣ የተጠመቀ ተቀድቶለት እየበላ ላደገ የኔ ብጤ ከባድ ነው፡፡ እናም ሳይወድ በግድ ወደ ኢንተርኔት ገብቶ ማን እንዳበሰለው የማይታወቅ መረጃ ጎልጉሎ ያጎርሰናል፡፡

ሦስተኛው ምክንያት ደግሞ ስለ ውጭ ሀገር ሰዎች እና ስለ ውጭ ሀገር ጉዳዮች ማውራት እና መዘገብ እንደ ነጻ መሬት ስለሚቆጠርም ነው፡፡ የውጭ ሀገር ሰዎች እና ጉዳዮች ነገር ከማን ኛውም ዓይነት የፖለቲካ አመለካከት ተጽዕኖ ነጻ ናቸው፡፡ እገሌን ደገፍክ ወይንም እገሌን ተቃወ ምክ አያሰኝም፡፡ አንዳንዴም እዚህ ሀገር የመንግሥት ያህል ዐቅም ያላቸው ቱባ ግለሰቦችም አሉ፡፡ እነዚህ ቱባ ግለሰቦች አስቀየመን ብለው የሚያስቡትን ሁሉ ልክ ሊያስገቡ ይችላሉ ተብለው ይታማሉ፡፡

እናም ጎመን በጤና ለመብላት ሲባል ማንም የማይከራከርባቸውን የውጭ ሀገር ሰዎች እና ጉዳዮች ማቅረብ ለጋዜጠኞች ነጻ ቀጣና በመሆናቸው ሁሉም ወደ እነርሱ ሳይዘምት አይቀርም፡፡

አራተኛው ደግሞ በእንግሊዝኛ የማሰብ ችግር ነው፡፡ አንዳንድ ጋዜጠኞች በእንግሊዝኛ እያሰቡ ነው በአማርኛ መናገር የሚፈልጉት፡፡ በተለይም ይህ ችግር በስፖርት ጋዜጠኞች ይብሳል፡፡ ፍቅሩ ኪዳኔ የፒያሳ ልጅ በተሰኘው መጽሐፉ እነ ይድነቃቸው ተሰማ እግር ኳስን በኢትዮጵያ ሲያስፋፉ እና ሕጉን ሲያመጡ የአማርኛ ትርጉም ለማግኘት ይደክሙት የነበረውን ድካም ነግሮናል፡፡ እግር ኳስን በአማርኛ ለማቅረብ፡፡

ይህንን ያልሰሙ አንዳንድ ጋዜጠኞቻችን ግን ደብል ኳስ፣ ፓስ አደረገ፣ ሚድ ፊልድ ላይ የሚጫወተው፣ በራይት ዊንግ ያለው፣ ኮምፕሌት ፓስ ነው፣ ኳስ ኮንትሮል ማድረግ፣ የሚሉት ቃላት ሁሉ ሀገርኛ ትርጉም ጠፍቶላቸው ነው? አንዳንዴማ ምክንያቱም ማለት ተረስቶ «ቢኮዝ» የሚባልበትም ጊዜ አለ፡፡

እና ወዳጆቼ ዕጣ ፈንታችን ምን ሊሆን ነው፡፡ ኤፍ ኤሞቻችን በአብዛኛው ዳያስጶራ እየሆኑኮ ነው፡፡ ምሁሮቻችንን አጣን፣ ወጣቶቻችንን አጣን፣ ቅርሶቻችንን አጣን፡፡ ምነው በዚህ ቢበቃን፡፡ ደግሞ ኤፍ ኤሞቻችንን እንጣ እንዴ፡፡

እባካችሁ ኤፍ ኤሞቻችንን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የቀማችሁን ሰዎች ስለማርያም ብላችሁ መልሱልን፡፡ የሀገሬን ጉዳይ፣ የሀገሬን ሃሳብ፣ የሀገሬን ሰዎች፣ የሀገሬን ታሪክ፣ የሀገሬን ታዋቂ ሰዎች፣ የሀገሬን ዜማ፣ የሀገሬን መረጃ ልስማበት፡፡ እባካችሁ ኤፍ ኤሞቻችንን መልሱልን፡፡

ኢትዮጵያዊ ሊነገረው እንጂ ሊነገርለት አይችልም ያላችሁ ማነው? ኢትዮጵያዊ ሊሰማ እንጂ ሊሰማ( ሰ ይጠብቃል) አይገባም ብሎ የፈረደ ማነው? ኢትዮጵያዊ ሊታሰብለት እንጂ ሊያስብ አይችልም ያለ ማነው?

ኒውዮርክ ጎዳና ላይ መኪኖች ተጋጭተው መንገድ መዘጋቱ ምን ይፈይድልናል? እዚህ ሃያ ሁለት ተጨናንቆላችሁ የለም እንዴ? እገሊት የተባለቺው ዘፋኝ ሆሊውድ ውስጥ በሚገኝ አንድ ምግብ ቤት ገብታ የአንድ ሺ ዶላር ራት በላች ብሎ ማውራት ድኻውን ከማስጎምጀት ያለፈ ጥቅሙ ምንድን ነው? እገሊት ከእገሌ ጋር በፍቅር ወደቀች፣ እነ እገሌ ሊጋቡ ነው፣ እገሊት ርጉዝ መሆንዋ ታወቀ፣ እገሌ ደግሞ አንድ ልጅ ከአፍሪካ በማደጎ ሊወስድ ነው እያሉ አዲስ አበባ ተቀምጦ እንግሊዝ እና ካሊፎርንያ ላይ መፎነን ምን የሚሉት አባዜ ነው፡፡

ኸረ ስለፈጠራችሁ ኤፍ ኤሞቻችንን መልሱልን፡፡ ያለበለዚያማ እዚህ ሀገር FM የሚለው ምሕፃረ ቃል ትርጉሙ foreign media ሊሆን እኮ ነው፡፡

እስኪ አንድ አቦ ሰጠኝ ግጥም ልስጥና የሀገሬ አዝማሪ ይቀበለኝ

ኤፍ ኤሜን ያያችሁ

አላየንም

ጋዜጠኞች እባካችሁ

አላየንም፡፡ አላየንም፡፡